በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከሜይ 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከሜይ 11-20 እና ከሜይ 21-31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

**እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ** ...- 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ...- 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ...- 3 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ...- 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ...- 3 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ...- 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ...- 4 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ...- 5 -

...- 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ...- 5 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ...- 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ...- 7 -

እ.ኤ.አ ከመይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ...- 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሜይ 21-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ...- 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ...- 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ...- 9 -



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በደቡብ፣ በመካከለኛው እንዲሁም በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እና ክምችት የነበራቸው ሲሆን፤ በብዙ ስፍራዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው መካከል በአርባ ምንጭ 34.9 እና 38.0፤ በቢሾፍቱ 41.0፤ በነገሌ 45.1፣ 31.9፤ በአዋሽ አርባ 30.0፣ በብላቴ 46.6፤ በቦሬ 39.2፤ በቡርጂ 39.0፤ በዲላ 36.4 እና 38.2፤ በዶሎመና 30.2 እና 40.1፤ በገዋኔ 43.3፤ በቡሌ ሆራ 32.8፣ በኮንሶ 38.4 እና 30.0፤ በሞያሌ 85.4፤ በአዳማ 36.1፤ በወላይታ ሶዶ 35.7፤ 32.2 እና 55.0፣ በያበሎ 31.6 እና 36.5፤ በሂርና 36.4 እና 37.0፤ በኮምቦልቻ 46.8፤ በጨለንቆ 40.2፤ በዶሎ ኦዶ 96.1 እንዲሁም በ ኮምቦልቻ( ምስራቅ ሀረርጌ) 46.8 በሚ.ሜ ይገኙበታል።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከሱማሌ ክልል ዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ ኖጎብ፣ ኤርር እና ሲቲ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ ከቤንሻንጉልጉሙዝ ክልል አሶሳ፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ሲልጤ፣ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ ካምባታ፣ጠምባሮ እና ሀላባ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ኮንሶ፣ ጌደኦ፣ ወላይታ፣ደራሼ፣ ቡርጂ እና አሪ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በንች ሸኮ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ31-160 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ4-10 ቀን ያህል ዝናብ ያገኙ ሲሆን፣ ከኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ቄለም ወለጋ፣ሆሮ ጉዱሩ፣ ቡኖ በደሌ፣ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን ሸዋ፣አዊ ዞን፣ ከአፋር ክልል ቂልበቲ፣ፈንቲ እና አዉሲ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል ፋፋን፣ ጀረር፣ ዶሎ እና ቆራሄ ዞኖች፤ ሁሉም የትግራይ ክልል ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ከማሺ እና የማኦኮሞ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ አኝዋክ እና ንዌር ዞኖች ላይ ከ3-30 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-3 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲገመገም ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀራር፣ ኤረር፣  ዶሎ፣ ኖጎብ፣ ቆራሄ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን፣ እና ዳዋ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣  ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ) ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቂልበቲ፣ አዉሲ፣ ፈንቲ፣ ጋቢ እና ሀሪ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ማዕከላዊ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ጎፋ፣ ሀላባ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ሁሉም የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ እና  ኮንታ ዞኖች እና ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ሀረሪ፣ ድሬ ዳዋ እና አዲስ አበባ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡


በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፤ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ38-41.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል1) ፡፡





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066    ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት የበልግ አብቃይና ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የነበረው እርጥበት ቀደም ብለው ለሚዘሩ የመኸር ወቅት ሰብሎች ማሳን ለማዘጋጀትም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ከዚህም በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜን ለመጨመር፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4) ፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣አዋሽ፣የላይኛው እና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌ፣ በጥቂት ላይኛው አባይ እንዲሁም ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይህንም ሁኔታ ለከርሰ ምድር እና ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት መጎልበት አውንታዊ ጎን እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5)፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በምስራቅ፣ በመካከለኛው በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎቻችን ያመላክታሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ፣ እንዲሁም በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ስርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 6 )፡፡ በተጨማሪም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች እንዲሁም በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በርካታ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉባቦር፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ) ዞኖች፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ባሌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ ዞን እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ካማሺ፣ መተከል እና የማኦ ኮሞ ልዩ ዞን፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ባስኬቶ፣ ኮንሶ፣ አማሮ፣ ኣሌ፣ ጎፋ እና ወላይታ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ስልጤ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፣ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ የኢታንግ ልዩ ዞን እና ንዌር ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ሊበን፣ ዳዋ፣ ሸበሌ እና ኤረር ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ ዳዋ እና ሃራሪ ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት የሚኖራቸዉ ሲሆን(ካርታ 6)፣ በተጨማሪም ከአፋር ክልል ቂልበቲ፣ ፋንቲ፣ አውሲ፣ ሃሪ እና ገቢ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል ጀረር፣ ኖጎብ፣ ዶሎ፣ ቆራሂ እና አፍዴር ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ባሌ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ደቡብ ኦሞ ዞን፣ ከአማራ ክልል ዋህግምራ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሜይ 11-20, 2024
የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከመይ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በሜይ ሶስተኛው አስራ አንድ ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በምዕራብ አጋማሽ ላይ ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በደቡብ፣ በመካከለኛው፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ለዝናብ መፈጠር አመቺ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና በተለይም በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 7)



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከሜይ 21-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ በሜይ ወር ለሚከናወኑ የበልግ ወቅት የግብርና ስራ እንቅስቃሴን በተጠናከረ ሁኔታ ለማከናወን አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ሲሆን የሚገኘውም እርጥበት ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ቀደም ብለው የሚዘሩ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራትና ዘግይተው ለሚዘሩ የመኸር ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ ለአርብቶ አደርና ለከፊል የአርብቶ አደር አካባዎች ለዕጽዋት ልምላሜ፣ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው አካላት ከአርሶ አደሮች ጋር በጋራ በመሆን የሚገኘውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የግብዓት አቅርቦቱን በውቅቱ በመጠቀም የእርሻ ሥራውን በተሟላ መልኩ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል በእንዳንድ ቦታዎች የሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት በሰብሎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊያስከትል ስለሚችል፣ የአፈር ጸባያቸው ውሃ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በማያሰርጉና ረባዳማ በሆኑ ቦታዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛት እንዳያስከትል የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሜይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በአባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ እና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት የሚጠበቅ ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታ ከአፋር ደናክል፣ ከኦጋዴን፤ ከተከዜ ተፋሰሶች በስተቀር የተቀሩት ተፋሰሶች ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል። ይህም ሁኔታ በየተፋሰሶች የሚገኙት የውሃ አካላት የተሻለ የውሃ መጠን እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ለመስኖም ሆነ ለሀይል ማመንጫነት የሚያገለግሉ የግድቦችን የውሃ መጠን የሚያሻሽል በመሆኑ፤ ይህንኑ እድል ለመጠቀም የሚያስችል የቅድመ ዝግጅት ተግባራትን ከወዲሁ ማከናወን ያስፈልጋል።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et